# ከእባቡ ጊንጡ፤ ከወያኔው ደቀመዝሙሩ

ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በሀገራችን የሚታየው ሁኔታ የሚያበረታታ ሆኖ በመገኘቱ የተስፋ ብርሀን ደመቅ ብሏል። ሕዝብ ጭቆናውን ተቀብሎና  በወያኔ ተሸንፎ ጸጥ ለጥ ብሎ እየተገዛ ነው የሚለውን ንቀት አዘል ግምጋሜ ሐሰት ውሸት እያለው ነው። ብዙዎች ባለው ትውልድ ላይ ተስፋ ቆርጠው አያሌ የሒስና ብስጭት ንግግሮችን አድርገዋል። ዛሬም ቢሆን ያለው ትውልድ በወያኔ ወጥመዶች ገብቶ የተሰናከለ ነው የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም።

የቀቢጸ ተስፋው መነሻ ቢገባንም ሀቁ ግን ሌላ ነው። የዛሬው ትውልድ የራሱ ወቅቱ ያሳዘለው ድክመቶች ቢኖሩትም ሀገርም ለማዳን የሚታገል መሆኑ ላይ ጥርጣሬ ሊኖር አይገባም። መለስ ብለን ብናይ ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ በተቃውሞ ሰልፍ ተሰልፎ መስዋዕትነትን የከፈለ ነው። ኢአግ - የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር - ተብሎ ትጥቅ ትግል ሲጀመርም አለን ብሎ የተሰለፈና የተሰዋው የዛሬው ትውልድ አባል ነው። በ1997 ኡ የምርጫ ሂደትም ግንባሮቹን በመደገፍና መስዋዕትነትንም በመቀበል የሚመራና አርአያ የሚሆን ካለ የሚታገል መሆኑን በደሙ አጅቦ ግልጽ አድርጎታል። ዛሬም በዚህም በዚያም በሚደረጉ ተቃውሞዎች ውስጥ ወጣቱ አለበት። በአንጻሩ ደግሞ፤ ሕብረተሰብ ውጥንቅጥ ነውና እንደ እናት ማህጸን፤ እናት ሀገሩን ከድቶ ከዘረኛው ወያኔ ጎን የተሰለፈ፤ ለገንጣዮች ሰለባና ጭዳ የሆነና ለባዕዳንም  ሰላይ ቅጥረኛ የሆነውም ወጣት አለ። በአልባሌ ጠባዮች ተበክሎ የባከነውን ሳንረሳም ማለት ነው። ወጣም ወረደም ግን ኢትዮጵያ ከሰፈሩባት ዲያብሎሶች የምትገላገል ከሆነ ወጣቱ ለትግሉ መሰለፍ እንዳለበት መታወቅ አለበት። የአሜሪካ ወጣት ወታደሮች መጥተው ነጻ አያወጧትም።  በስደት ላይ ያለውም ነጻ አውጪ ሊሆን  እንኳን ቢቃጣው ትግሉ በሀገር ቤት ወጣቶች ደማቅና ቆራጥ አጀብን ካላገኘው ፈቅ የሚል አይሆንም። ይህ ደግሞ በየካቲት 66ም የተከሰተና ከዚያም በኋላ ያየነው ነው። ለዚህም ነው ወጣቱን -- አብዛኛው ዜጋ ነውና፣ ናትና-- ወደ ትግሉ መሳብ መቻል ያለብን፤ በትግሉ ተሰላፊ ማድረግ ያለብን:: በዚህ መስክ ወጣቱን ከጥቅም ውጪ፤ ግለኛና ሽንፈተኛ ሊያደርግ ከሚጥረ ወያኔ ጋር ግብግብ መግጠምና አምርረን መታገል አለብን።

በሁለገብና በሰላማዊ ትግል መሀል አለ የተባለው ልዩነት--በወያኔ ተፈጥሮ በተለጣፊዎች የተስተጋባው-- ውሎ አድሮ እየተወገደ ነውናም በአሁኑ ጊዜ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ዜጎች በተቃውሞ ስልፍና እንቅስቃሴ እየተሳተፉ ናቸው። ቀስ በቀስ እንዲሉ በተደጋጋሚ ጥረትና ተጨባጭ ተሳትፎና ሙከራ ብዙሀኑ--በተለይም የፖለቲካ መሪነትን ሚና መያዝ ፈላጊዎች-- ከፍርሃታቸው ይላቀቃሉ። ለዚህም ነው በሀቅ ጸረ ወያኔ የሆኑትን መደገፍና ማበረታታት የሚገባው። ወያኔ በበኩሉ ታሰርን ተጠቃን እያሉ ትግሉን ሰርገው ገብተው የሚያሳፍኑ ዳግማዊ ክህደቱ-ልደቱዎችን በስልት አዘጋጅቶ አሰማርቷል--ጋዜጠኛም ድርጅት መሪም ሆነዋል። ቀደም ሲልም ትግልን ሲያደናቅፉ የነበሩትን እስትንፋስ ሰጥቶ በየድርጅቱ አስገብቷል። ቀጥይ ሆኖ የቆየው የሙስሊም ዜጎች ሰልፍና አሁንም በሌሎች እየተሞከረ ያለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ራሱን መጠበቅ እንዳለበት ግልጽ ነው:: ይህም ህጋዊ ሆነው አዲስ አበባ ቢሮ ያልከፈቱትንም ይመለከታል። ተቃዋሚ መስለው በወሳኝ ወቅት ትግሉን ለወያኔ አጋልጠው የሠጡ - አዎን የከዱ-- ዛሬም በተቃዋሚው ጎራ አሉ። ይህ መቀጠል የለበትም። ነገ ደግሞ ትግሉን ሲያይል እንደገና --በፍርሐትም ሆነ ለጥቅም-- ይከዳሉ፤ ይጎዳሉ። ከእባቡ ጊንጡ እንደተባለው ከወያኔዎቹ ብሶ የወያኔን ህገ መንግስት ተብዬ ካልተቀበሉ ጋር መነጋገር አልፈልግም ያለና ወያኔ ስልጣን ሲይዝም ተሿሚ የነበረና ህብረትንም ለማፍረስ ብዙ አስተዋጾ ያደረገ ግለሰብ በምሳሌነት ይጠቀሳል። ባጭሩ ትግሉና ድርጅቶችና ተቃውሚዎች ሁሉ በጀመሩት ትግል ሊገፉና ሊጠናከሩ የሚችሉት ራሳቸውን ከታወቁ ትግል አደናቃፊዎች ሲያርቁና ሲያጸዱ ነው። ይህን ወሳኝ ማሳሰቢያ በግለሰቦች ላይ ዘመቻ አድርገው የሚወስዱ ደግሞ ስህተትን ይፈጽማሉ--ከታሪክ ተማሩ ሲባሉ መልሳቸው እምቢ ነውና። መናገር መልካም ነው፣ ማዳመጥ ይበልጣል ልንላቸው እንገደዳለን::

ከወያኔ ባልተናነሰ የሕዝብን ትግል እያደናቀፉ ያሉት የይፋም ሆነ ስውር ደቀመዝሙሮቹና ቅጥረኞቹ ናቸውና ታጋይ ክፍሎች መውሰድ ያለባቸውን ጥንቃቄ መረዳትና ማወቅ አለባቸው። በረጅሙ መራራና ጎጂ የትግላችን ሂደት ብዙ እንቅፋት አጋጥሞን በአብዛኛውም ጊዜ ጊንጦቹ ከትግሉ መሀል የፈሉ መሆናቸውንም መታዘብ ችለናል፤ ተቆጭተናልም። ኮሶ ሳይመር አያሽር ተብሏልና ባይጥመንም የደረሰብንን ጉዳት ማጤን

መቀበል፣ በዘመኑ ቋንቋ እንዴት እንደተበላን ማወቁ በጣም ጠቅሚ ነው። ወያኔ የሙስሊም ዜጎቻችንን ትግል ከሌሎች ድጋፍ እንዳያገኝ ያካሄደው ርኩስ ቅስቀሳ ጸረ ወያኔ ነን ባዮቹንም አይቀር ማደናገሩ እያታየ ያለ ነው። ወያኔ ህጋዊና በርግጥም ጸረ ወያኔ የሆኑትን ድርጅቶች ለመከፋፈል ውዳቂም ሆነ ረቀቀ ሊባል በሚችል መንገድ ሲጥር ዓመታት አልፈዋል--አሁንም እየቀጠለበት ያለ ነው። ለወያኔ ዋና ጠላት ደግሞ የፈረደበት አማራ ነውና አማራው ላይ ሌላው እንዲነሳ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም:: ደቀመዝሙሮቹ ደግሞ ከእባቡ ጊንጡ ሆነው አማራውን እየነድፉና እያጠቁ ናቸው -- አማራውን የማጥቃቱ ዘረኛ ዘመቻም ከቶም አልበረደም። በጸረ አማራው ዘመቻ ጸያፍ ሚና ሲጫወት የቆየው የሻዕቢያ ሰላይና ደራሲ ጋዜጠኛ ነን ባይ አማራው ላይ ኦሮሞውን ለማነሳሳት ያደረገው በቅርቡ በሰፊው ዳግም ተጋልጧል:: ይህም ደግሞ ወዳነሳነውና ማንሳት ወዳለብን አቢይ ጉዳይ ይወስደናል:: ማለትም ወዳጅና ጠላትን መለየት ወሳና ቀዳሚ መሆኑን በተመለከተ ማለት ነው። በተደጋጋሚ በሕዝብ ላይ በደል የፈጸሙትን፣ የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን፣ ከሀዲና አንጃ ሆነው ደም ያፈሰሱና ያስፈሰሱትን፣ ትላንት ወያኔ ሆነውና ዛሬ የአንድ ብሄረሰብን የበላይነት የሚያቀነቅኑትን፣ ታጋይና ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን ለማፍረስ የተሰለፉትን ወዘተ ሁሉ በዕይታ ማስገባትና መጠንቀቅ ተገቢ ነው። በርግጥ ሰው ሊቀየር ይችላል፣ ግን በሀቅ ግለ ሂስ ያላደረገ ወይም ንስሐ ያልገባው ግን በአፉ በሚለው ብቻ አምኖ ልብን መስጠትና በርን በርግዶ ግባ ማለት ጎጂ ሞኝነት ነው::

በአሁኑ ጊዜ የሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቅሴ የፍርሐትን መጋረጃ እየከፈተ በመጀመሪያ ደረጃ ቢሆንም መጣሁ እያለ ነው። ከወዲሁ ድጋፍ ያስፈልገዋል። በባዕድ ሀገር ያሉትም ይህን የሀገር ውስጥ  ድጋፍ የትም አይደርስም በሚል መዝጋት ሳይሆን ትግሉን ቀጥሏል ብለው መድገፍ አለባቸው--በተለይም የሁለገብ ወይም የትጥቅ ትግል አቀንቃኞች ተጨባጭ እንቅስቃሴ ላም አለኝ በሰማይ መስሎ ባለበት። ይዘቱ በምንፈልገው ደረጃ፣ ብስለትና ጥንካሬ ደረጃ ገና ባይሆንም መከሰቱን መደገፍና ማበረታት አስፈላጊ ነው። ከወያኔ የባሱ ጊንጦች በትግሉ ላይ ፈልተው እንዳሉ፣ የወያኔ ተለጣፊዎችና ደቀመዝሙሮች እንዳበደ ውሻ ታጋዮችን ይናከሱ ዘንድ መለቀቃቸውን (ከበቂ ድጎማ ጋር) ማወቅ መገንዘብ ይገባናል። ወያኔ የሞት ሽረት ጉዳይ ስለሆነበት 24 ሰዓት ሳይታክት

የህዝብን ትግል ለማደናቀፍና ለማጥፋት ይጥራልና እንጥለዋለን የሚሉት ክፍሎች ደግሞ ከወያኔ በበለጠ መታገልና መረባረብ አለባቸው ማለት ነው። ለዚህም ነው ጸረ ወያኔ ትግላችን ዳግም ዳግ፣ ሰለባ ሆኖ ድሉን መቀማት የሌለበት። ተቃውሞስ እንዴት? ሰልፍስ እንዴት ይዘጋጃል? በአንድ ቦታ የሚጀምር ትግል ሀገር አቀፍ ሊሆንስ እንዴት ይችላል? ለዚህ ሁሉ በቂ ተመክሮ አለ። መማር ግን መፈለግና መቻል አለብን:: ይህ ዕንዳይሆን ደግሞ ወያኔና ደቀመዝሙሮቹ -- ቅጥረኞቹ _ ያለፈውን ተመክሮ ማክቸልቸልና በታገሉትም ላይ ዘመቻ ማካሄድ ዋናው ተልኮአቸው ሆኗል። በሀገር ቤትና በውጭ ሀገርም ለምሳሌ በኢሕአፓ በዚያን ጊዜ ትውልድ ላይ የተከፈተው ሰፊ የማጥላላትና የማስጠላት ዘመቻ ምሳሌ ነው። ወያኔም ሆነ ተለጣፊዎቹና አፍራሾቹ ሽንኩርት በባሕሪው ይሸታል መባል ሲያንሳቸው ነው ማለት ነው።

የትግል ተመክሮ በአሉታዊው ሆነ በጹጋው በርካት ያለ አለን። ዛሬ ተቺና ወቃሽ ሆነው መድረክ ሊያጣብቡ የሚባዝኑት ግን ይህን ተመክሮ ሲያወግዙ ምን እንደነበርም የሚያውቁ አይደለም። የተበላሸ ታሪኩን/ታሪኳን ለመሸፋፈን ሲለፍፉ ሆነ ሲጽፉ ወይ ጉድ ብለው የሚያወግዙ ሳይሆኑ የሚያወድሱትን ማሞካሸት ልምድ የሆነ ይመስላል። ውዳቂዎቹ ደግሞ ነጋ ጠባ--ብዙዉን ጊዜ በወያኔ ድጋፍ-- ሲጮሁ ወይም ሲጽፉ አጀቢው ያው ግም ለግም አብረህ አዝግም ነውና ሌሎች ወንጀለኖች፤ በታኞችና ወያኔዎች ናቸው። ኢትዮጵያ የመቶ ዓመት ታሪክ ብቻ አላት የሚለውን ኢትዮጵያ የፈጠራ ወሬ ናት በሚሉትና  ትውልድ በጸረ ኢትዮጵያ ባዕዳን ታጅቦ ሲስተጋባ ቆይቷል። የአረመኔው መንግስቱን አገዛዝ በታገለው ትውልድ ላይ ዛሬ በተለይ በወያኔ አጋፋሪነት እየተካሄደ ያለው ጸያፍ ዘመቻ ምስክር ነው::  በዚህም በዚያ የወያኔና ጭፍሮቹ ግብ ያታገሉትን ድርጅቶች መወንጀልና ማስጠላት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የዛሬው ታጋዮች ካለፈው ተመክሮ እንዳይማሩ አግዶ ለወያኔ ሻጥር ሰለባ ለማድረግ ነው። ያለፈውን ተመክሮ በሚገባ ቢያጤኑ ኖር ቅንጅትም ሕብረትም በወያኔ ቅጥረኞችና በቡከኖቹ ባልፈረሱ ነበር:: የደረሰውን ነው እየደገሙ ያሉት:: ገገሮዎች ሁሌም ሕዝብን ይከፋፍላሉ፤ ከ አገዛዝ አገዛዝ ክፋቱ ቢለያይም። የወያኔን ክፉ የሚያደርገው ገና ሲቋቋም ጀምሮ ግቡ ኢትዮጵያን ማፍረስ መሆኑ ነው። በዚህም ስምሪቱ አጃቢዎች ማግኘቱ ነው። ይህን እንዴት መቋቋም ይገባል? ወያኔ

በቀደደው ቦይ ፈሶ በክፍፍል መሰረት መሰባሰብና መፈራቅቀ? በብሄረሰብና በሃይማኖት ልዩነት መናቆር? ኢትዮጵያዊነትን ማደብዘዝ ወይስ ስንጥቅ በታየበት መለሰንና ማጠናከር? ትግልና ፖለቲካን እንደ ንግድ መያዝ? ጀግና የጠፋ ይመስል አስመሳዩን ሁሉ ሀገር ወዳድ ማለት? ጥያቄው ወሳኛና አቢይ ነው። የነቂሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ እንዳንባል መጠንቀቅ አለብን ማለት ነው::" በአሁኑ ጊዜ እየተፋፋመ ያለው ትግል በዚህም በዚያም ከተጠናከረ የምንፈልገው ሕዝባዊ አመጽ እውን ሊሆን ይችላልና መደገፍ አለበት።

በሌላ በኩል ግን የትግላችን አጋርና ግብ ማንና ምን ይሁን በሚለው ላይ በቂ ግንዛቤ ያስፈልጋል። የሕዝባችንን ትግል በባዕዳን ወይም በሌላ የሚረዳና የሚታደግ ነው ብለን ማሰብ የለብንም። ዛሬ ባዕዳን ወይ ወያኔን ወይ ገንጣዮችን ወይ ቅጥረኞቻቸውን እንጂ ሀገር ወዳዶችን ከቶም ካልተገደዱ አይረዱም። ከሰጡም ግባቸው ሌላ ነው ማለት ነው። የግብጽን ስራና ሴራ ይመለከቷል። ለዚህም ነው ሕዝብን ማደራጀትና በራስ መተማመኑ መቅደም ያለበት። በራስ ሕዝብ አቸናፊነት ላይ ጥርጣሬ ካለና ባዕድ አምልኮ ከሰፈነ የሀገር ስርየት ይርቃል። ይህንንም መገንዘብ ይበጃል። ግብ ማወቅም ደግሞ አቅጣጫን ያስይዛል። ትግል ለኢትዮጵያ አንድነት ነው:: ገንጣይና የአንድነት ሀይሎች በጋራ የሚሰለፉበት ሁኔታ የለም። እንታገልና ሕዝባችንን የምንለው "ኋላ መብቱ ተጠብቆ ለመገንጠል ወይ ለሌላ ሕዝበ ውሳኔ ያድርግ" ለሚሉት ከኤርትራ መሰል ነጻነት ወይስ ባርነት አስመሳይ ውሳኔ ህዝብ በኋል የምንሞኝላቸው አይሆንም። ዳግም አንጃጃልም። ኮሶ በኮሶ ይሞታል ነው ነገሩ። ነቃ ብሎ ጠላትና ወዳጅን ለይቶ መታጉሉ መቅደም አለበት። ነጋ ጠባ እያደናገሩንና የከፋፈሉንንና የጎዱን መልሰን መልሰን ማቀፍና መሪ ማለቱ ሀገርንና ሕዝብን ይጎዳል። የተጀመረው ጸረ ወያኔ የሚደገፍና የሚበረታታ ተቃውሞ ራሱን ከጥቃት መጠበቅ ግዴታው ነው። ይህም የሁሉ ዜጋ ሀላፊነት ነው:: በሁለ ግብ ትግል እንሰማራለን ያሉትም ሁሉ በተጨባጭ የትግል ፍንጭ ማሳየት አለባቸው። ሌላውን መተቸቱ በአፍ ሳይሆን በተግባር ቢሆን ይመረጣል ማለት ነው:: ሁሉም ዓይነት ትግል በየፊናውና ቢቻል ደግሞ ተባብሮና ተቀናጅቶ ቢካሄድ የወያኔ ዕድሜ ያጥራል። በዚህ

መስክ ደግሞ አሁንም ቢሆን ድርጅቶች ሊተባበሩ የሚችሉበትን ጥረት ፍለጋ ማድረግ እንዳለባቸው ማሳሰቡና መቀስቀሱ መቀጠል ያለበት ነው።

ዕውቀት ሀይል ነው ። የዛሬውን ትግል ለማሳካት ያለፈውን ደም የፈሰሰለትን ትግል ታሪክ እንወቅ። ታሪኩን የረሳ ስህተትን ይደግማል ነውና ዛሬ በጸረ ወያኔው ወሳኝ ትግል ላይ ባለንበት ወቅት ከ እባብ በባሱ ጊንጦች ከወያኔ በባሱ ደቅመዝሙሮቹና ቅጥረኞች ሳንደናገር ሀገር አድን ትግልን ከግቡ ለማድረስ በጋራ እንታገል። ሌላ ጥሪ ሌላ መልዕክት የለም።